# እናት !!



ታንኩን በጎራዴ፣ የምትመታ፤

በቦምብ በመርዝ ጭስ፣ ሳትፈታ፤

እሳት ለብሳ፣ ምሳ ጉርጓዱን፤

ኢትዮጵያን ብላ፣ እናቷን፤

ያስቀድመኝ፣ ብላ ፈጥና፤

ቶሎ ደርሳ ፣ ድምበር ሆና፤

ማገር ሆና ፣ ነዳ ደብና፤

ግንባር ለግንባር ፣ ጠላት ገጥማ፤

ሳትፈራ ፣ ሳታቅማማ፤

ሰላቶውን ፣ አስደንብራው፤

እየነዳች እንደመንጋ ፣ አስገብራው ።

ኃያልናቸው ፣ እሳቶች፤

ሰው አይደሉም ፣ መላዕክቶች፤

የተሰኙት ፣ ማን መሰለህ ?

# እናት !!

ለጣሊያነም ፣ አልበጀን፤

ለእንግሊዚም ፣ አልተመለስን፤

ተከናንቦ ሸማውን ፣ የውርደቱን፤

ካባውን ደርቦ ፣ የቅሌቱን፤

አልሰማህም ምርኮኛውን ፣ መመስከሩን እውነታውን ?

ተመልከት ፋይሉን ፣ መዛግብቱን፤

ታሪኩን ፣ የቀድሞውን ።

እናቴ የኔ ክብሬ ፣ መመኪያዬ፤

የኔ አምባ የኔ ቁዬ ፣ መኖርያዬ፤

ጥፍር አርጋ ፣ መቀነትቷን፤

ተቀብላ ሲቃ ፣ መከራዋን፤

ወጊድ ብላ ፣ ሽንፈትን፤

አደረዋን የተውጣች ፣ ያቺ እማማ፤

ከራስዋ አብራክ በወጣ ደለንቱ ፣ ይኸው ታማ፤

# እናት !!

አንደበቷ ተለጉሞ ፣ እንደበቅሎ፤

አይኗ ጠፍቶ ፣ ተጠንቁሎ፤

ሲቃ ገብታ ፣ ታነባለች፤

ዛሬም ነገም ፣ ትጣራለች !!

ዛሬም ነገም ፣ ትጣራለች !!

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2012-05-17

ማስታወሻ :- የህ ግጥም ውድ ሕይወታቸውን ለእናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ለሰዉና አሁንም እናት አገራቸውን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ ትንንቅ ለተያያዙ እህቶችና እናቶች ይሆንልኝ ዘንድ ጽፌዋለሁ።